# ዶክተር አቢይና ለውጡ የት አሉ?

ግርማ በላይ (gb5214@gmail.com)

ናስሩዲን የተባለ የኛኑ መሰል ግብጻዊ አለቃ ገ/ሃና ነበረ፡፡ ብዙ ቀልዶች እንዳሉት ይነገርለታል፤ አንዳንዶቹንም አንብበናል፡፡ አንዱን እዚህ ላስታውስና ወደ ቁም ነገሬ ልግባ፡፡ ናስሩዲን ሦስት ኪሎ *ሥጋ* ገዝቶ ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ *ሥጋውን* ለሚስቱ ሰጥቶ ጓደኞቹ ጋር ሊዝናና ከቤቱ ወጣ ይላል፡፡ ሲመለስ *ሥጋውን* ካስቀመጠበት ያጣዋል፡፡ ሚስቱ ያንን *ሥጋ* ለእራታቸው ሠርታው እንደሆነና እንዳልሆነ ይጠይቃታል፡፡ እርሷ ግን "ድመቷ በላችው" ትለዋለች፡፡ ናስሩዲን ያኔ ይናደድና ድመቷን አፈፍ አድርጎ ሚዛን ላይ ያስቀምጣታል፡፡ ሲመዝናት ልክ ሦስት ኪሎ ትሆናለች፡፡ ሚስቱ ላይ አፍጥጦ "ስሚ አንቺ ሴትዮ! *ሥጋውን* ድመቷ በላችው ብለሽኛል፡፡ ድመቷን ስመዝናት ግን ሦስት ኪሎ አናቱ ላይ ሆነች፡፡ ስለዚህ የመዘንኩት በድመቷ ሆድ ውስጥ የሚገኘውን *ሥጋ* ከሆነ ድመቷ የት አለች? የመዘንኩት ድመቷን ከሆነ ደግሞ *ሥጋው* የት አለ?" ብሎ ያፋጥጣታል፡፡ መልስ አልነበራትም፡፡ ለምን ቢባል *ሥጋውን* ሴትዮዋ ቅርጥፍ አድርጋ በልታው ነበረና፡፡

በሀገራችን እፍ እፍ የተባለለት ለውጥ መጣ ተባለ፡፡ ብዙዎቻችን በፍቅር ከነፍንለት፡፡ "የማያዛልቅ ባል ቅንድብ ይስማል" እንዲሉ ሆኖ "ልዘላችሁ ወይንስ ልቀፋችሁ?" ይለን የነበረው የለውጡ ሞተር ዘዋሪ ኢሕአዴግ-ሠራሹ ዶክተር አቢይም በወረት ፍቅር ብዙዎቻችን የምንሆንለትን እስክናጣ ድረስ ገና በቅጡ ባልተለማመደበት የመሪነት ግርማ ሞገሥን ማሳመሪያ ንግግሩ አናወዘን፡፡ "በርሱ የመጣ ባይኔ መጣ" እስክንል በሞኝ ፍቅር ሆድ ይገትር ዓይነት "ፎንቃ" አብዛኞቻችን ተዘረርንለት፤ ከአምላክ ባልተናነሰ እግሩ ሥር ወድቀን ሰገድንለት፤ ውስጡን ስለሚያውቅ በከንቱነታችንና በጅልነታችን እርሱም ታዝቦን በሆዱ ከት ብሎ ሣቀብን፡፡ የሀገራችንን ስም ለመጥራት እንኳን የሚጠየፉ መሪዎች በተቀመጡበት ወንበር ላይ ተቀምጦ በደቂቃዎች ውስጥ ሠላሣና ዐርባ ጊዜ "ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ" ሲል በርግጥም ልባችን ቢሠወርለት አያንሰውም - ይህን መሳይ ሰው ስንናፍቅ ብዙ ዘመን ባጅተን ነበርና፡፡ እርሱ ግን "ድመት መንኩሳ…" እንዲሉ ያደገበትንና የተሾመበትን ዓላማ ውሉን አልሳተምና ቀስ እያለ የጭቃ ጅራፉን ያኖጋው ጀመረ፡፡ ለውጡም ጥቂት እስረኞችን በመፍታትና በቃላት ድለላ ብቻ ሚሊዮኖችን በማፍዘዝ ተጠናቀቀና ለይቶለት ከነኮተቱ ገደል ገባ፡፡ በኬኛ ፖለቲካ የተጀመረው ጉዞ አሁን አሁን አማራን ወደ ማጥቃት ተሸጋግሮ የአማራን መብት ተከራካሪዎችን አከርካሪ መምታቱን ተያያዘው፤ የአማራ አለኝታዎችን ከየዘርፉ እየመነጠረ ማጥቃቱን ቀጠለ፡፡ አማራን ቤተስኪያን እንደገባች ውሻ ከያለበት ማሳደዱን በስፋትና በምልዓት ገፍቶበታል፡፡ መጨረሻውን ለማየት ያብቃን እንጂ የአቢይ መንግሥት ልክ እንዳባቱ እንደወያኔው መንግሥት የአማራን ዝርያ ከየቦታው በማጥራቱ ሥራ ላይ ተጠምዷል፡፡ ያደለው በሀገር ልማትና ዕድገት ላይ ይሠማራል - ይሄኛው ግን በዘረኝነት ላይ፡፡ "የዘሬን ብለቅ ያንዘርዝረኝ" ነው ተረቱም፡፡

ለውጥማ አለ፡፡ አምናና ታች አምና ብዙ ዜጎች እንደነገሩም ቢሆን እንጀራ ቀምሰው ያድሩ ነበር፡፡ አሁን ግን ጤፉ አራት ሽህ ብርን ሊነካ ጥቂት ብሮች ቀርተውታል፤ አምስት ሊትር የምግብ ዘይት ብር 450 ነው፤ ነጭ ሽንኩርት በኪሎ ከብር 160 በላይ ነው፤ ቀይ ሽንኩርት ሊያውም መተከል ቻግኒ ላይ (የሀበሻው) ብር 65 ነው፤ ኪሎ ሙዝ ብር 30 ነው፤ ብርቱካን ጣፋጩ ከብር 100 በላይ ነው፤ አንድ ጉርሻ እማይሞላ ፉርኖ ዳቦ ብር 3 ነው … አልቆልናል፡፡ ኑሮው የሰማየ ሰማያትን መስኮቶችና በሮች ጣጥሶ ሽቅብ ተወንጭፏል፡፡ ሽሮ ፈሰስ በተራ ቡና ቤት ሰባ ብር ስትባል ክትፎውን ስንት እንደሚሉህ አስበው - ከምናብህ ውጪ ነው፡፡ የእያንዳንዱ ዕቃና የአገልግሎት ዋጋ እንደሮኬት ተተኩሷል፡፡ እልም ያለ ገጠር ለመስክ ሥራ ብትወጣ ለውኃ የቀረበ መናኛ ጥብስና ዱለት እንደቅደም ተከተሉ ብር 80 እና 50 ነው፡፡ አንድ ሊትር የታሸገ ውኃ ብር 15 ነው፡፡ ተራ አልጋ በትንሹ 100 ብር ነው፡፡ ለሻይና ለቡና እንዲሁም ለአንድ ሁለት ሦስት ቢራ በያንዳንዱ 17 ደምርልኝና የቀን ወጪህን አስላው፡፡ የውሎ አበልህ ግን በቀን ግፋ ቢል 250 ቢሆን ነው - ባለ130ም አለ፡፡ ስንት ደመርክልኝ? ቁርስን በማሰብ ብቻ ዘለኸው ብር 350 ገደማ መጣልህ? አዎ፣ ሕዝብን በኑሮ ውድነት መጥበስ አንዱ የአቢይ መንግሥት ግልጽ ተልእኮ ነው - የሚገርመው ነገር ኑሮው በየደቂቃው ሲያሻቅብ አንድም የመንግሥት አካል ጅቦቹንና ዓሣሞቹን "ሃይ" አይልም፤ ምክንያቱም ሀገሪቱም ሕዝቡም ባለቤት የላቸውም - ያልታደለ ሕዝብ - ያልታደለች ሀገር፡፡ ደመወዙ ብር 1000 ሆኖ ኑሮው ብር 15000 የሚጠይቅበት ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ ናት፡፡ የቀን አበልህ ብር 130 ሆኖ በብር 400 እና 500 *ሥራህን* አከናውነህ እንድትመለስ የሚጠበቅብህ አእምሯቸው የመከነ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሞሉባት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት፡፡ እንደኛ በዕውቀትም በሀብትም ያጣ የነጣ ድሃን መግዛት ደግሞ አሣፋሪ ነው፡፡ ስለዚህ እነአቢይ ማፈሪያዎችና አሣፋሪዎች ናቸው፡፡ በመሠረቱ ሁለት በመቶ ለማይሆን ነጋዴና ሙሰኛ የመንግሥት ቴክኖክራት የቆመ መንግሥት 98 መቶኛ የሆነውን ድሃ ሕዝብ መብት ሊያስከብር አይችልም፡፡ የሀብታሞች አሽከር ነው፡፡

ለውጥ የለም፡፡ ኢሕአዴግ እያለ ለውጥ አይኖርም፤ በሽታን የፈጠረ መድኃኒትን ሊፈጥር አይችልም - እንዲያ ከሆነ አያዎ ነው - paradox፡፡ ኢሕአዴግ ራሱን በራሱ ተቃርኖ ፀረ-ኢሕአዴግ ሊሆን አይችልም - "ብዔል ዘቡል ብዔል ዘቡልን አያወጣም" እንዲል መጽሐፉ በኢሕአዴግ የተከሰተ ችግር በኢሕአዴግ አይፈታም፡፡ የጥገና ለውጥ ራሱም የሚታሰብ አይደለም፡፡ *ሥልታዊ* ማፈግፈግ

አደረገ እንጂ ኢሕአዴግ ለዬት ባለ ቅርጹ እየገዛን ነው፡፡ ፈረስ አልተቀየረም፡፡ ጋላቢ መቀየሩ ግልቢያን አያስቀርም፡፡ በአዲስ ጉልበት፣ በአዲስ ተረኛ ጋላቢ እየተጋለብን ነው፡፡ ለተወሰኑ ጥቂት ዣምንታት ጋብ ብሎ የነበረው እሥራትና ግርፋትም ከተወሰነ ዕረፍት በኋላ ተመልሶ እንደ አዲስ ፋሽን ተይዟል፡፡ የታሣሪዎች ማንነት መለዋወጥ እንጂ እሥሩ ከበፊቱም አይሎ ቀጥሏል፡፡ በፊት ታሣሪ የነበሩ አሁን አሣሪ ሆነዋል፡፡ በፊት ታሣሪ የነበሩ አሁንም በታሣሪነት የቀጠሉም አሉ፡፡ ዕድል ነው፡፡ ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም፡፡ የሁለት ወገን ተበዳይ፡፡ ያለፈውም የአሁኑም የሚያሰቃዩት ምስኪን - አማራ፡፡ ወደላይኛው እናንጋጥ፤ እንጸልይ፡፡

ለውጥ አለ፡፡ ለውጡ በፊት አማራ ባፈራት ቤትና ንብረቱ እየተሸቆጠቆጠም ቢሆን እንዲኖር ይፈቀድለት ነበር፡፡ በአሁኑ ‹ድንቅ› የለውጥ ዘመን ግን ኦህዲድና ኦነግ ይህን ዕድል ለአማራው ሊሰጡት አልፈለጉም - የሞኝ አሸናፊ ዱሮም መጥፎ ነው፤ የፈሪ ዱላም ዘጠኝ ነው፤ ፈሪ አያሸንፍ፤ ሞኝም አይርታ - ሲረታ እምቢ ብሎ ነውና፡፡ ስለዚህም ምድረ ኦነጎች በፈሪ ዱላቸው፣ በተሸናፊ-አሸናፊነት ሥነ ልቦናዊ ደዌያቸው እየተሰቃዩ አማራውን ከያለበት በማፈናቀልና ሀብት ንብረቱን በመቀማት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት ግን ሁሉም ኦሮሞዎች አለመሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት በጠላት ፕሮፓጋንዳ የተበከሉና ራሳቸውን ለውጭ ኃይሎች ፍላጎት መሣካት ያስገዙ ሆዳሞች ብቻ ናቸው፡፡ ጥይት በማይበሳው የ15 እና 20 ሚሊዮን ብር ዘመናዊ አውቶሞቢሎች በቅንጦት እየተዝናኑና የተምነሸነሸ ኑሮ እየኖሩ በባዶ እግሩ የሚሄድ አማራንና ኦሮሞን ለማጋጨት ሌት ከቀን የሚጥሩ የታሪካዊ ጠላቶቻችን ቅጥረኞች እዚሁ መሀል አዲስ አበባ በፌዴራሉ የኦህዲድ መንግሥት የሚጠበቁ አይሁዶች ኢትዮጵያን ባወጣች እየቸበቸቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር ለውጥ አለ፡፡ በዚህ ለውጥ ደግሞ ተጠቃሚው ብዙ ነው፡፡

ለውጥ የለም፡፡ ያ ሁሉ ወጣት ያለቀበት፣ ያ ሁሉ ሕዝባዊ ዐመጽ የተካሄደበት ለውጥ በአፈ ቅቤው ልበ ጩቤው አቢይ አህመድና ጓደኞቹ አማካይነት ተቀልብሷል፡፡ የነበረን ለማስቀጠል ያ ሁሉ ሰው መሞትና መሰቃየት አልነበረበትም፡፡ የነበረን የሊዝ ሥርዓት፣ የነበረን ዘረኛ ሥርዓት፣ የነበረን ሸፋፋና ወልጋዳ ሕገ መንግሥት፣ የነበረን የማያፈናፍን ቢሮክራሲ፣ የነበረን ከላይ እስከታች የተዘረጋ ሙስና፣ የነበረን አድልዖና መገለል፣ እግር ከወርች አሥሮን የነበረን የመመርያና የዐዋጅ ጋጋታ፣ ለስደትና ለርሀብ ዳርጎን የነበረን የዘረኝነት አገዛዝ፣ … ለማስቀጠል አልነበረም ያ ሁሉ ሕዝብ የታገለው፡፡ ለውጥ መኖር ከነበረበት ይሄ ሕዝብ ያልተሳተፈበትና የአድልዖ ሁሉ መሠረት የሆነው ህገ መንግሥት ተብዬው ነገር በሕዝብ ይሁንታ ቢለወጥ ነበር፡፡ የወያኔው ህገ መንግሥትም እንደህገ መንግሥት ተቆጥሮ አሥሬ “ህገ መንግሥት ተጣሰ፣ ህገ-መንግሥት ተጣሰ” እየተባለ መዘፈን የነበረበት ለውጥ የሚባል ነገር ባይከሰት ነበር፡፡ ሁሉም ነገር እንዳለ በቀጠለበት ሁኔታ ለውጥ አለ ማለት በዜጎች ደም መቀለድ ነው፤ በሕዝብ ላይ ማሾፍ ነው፤ የለውጥ ምንነትንም አለመረዳት ነው፡፡ አሁን የሚታይ ግልጽ ነገር ቂጥኛም ከውርዴ ሲጫወትና ሲዶልት ነው፡፡ ምድረ አማራ-ጠል ቀፈታም ከየአውሮፓና አሜሪካ ተጠራርቶ ኢትዮጵያን እንዴት መቃረጥ እንደሚቻልና አፍቃሬ ኢትዮጵያ የሆነውንና በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረውን በተለይ የአማራውን ጎሣ እንዴት ከምድረ ገጽ ማጥፋት እንደሚቻል በቤተ መንግሥት ቀን ከሌት ሲመክርና መመርያ ሲሰጥ ይውላል፤ ያድራል፡፡ ይህን እናውቃለን፡፡ ራሳቸውም እየነገሩን ነው፡፡ ስማቸውን እንደጊዜው ሁኔታ እየለዋወጡ ፀረ-ኢትዮጵያ አጀንዳቸውን በግላጭ እየተገበሩ ናቸው - እስስቶቹ፡፡ ጫካ ነበርን ባሉበት ጊዜ ብዙዎች ሀገር ወዳድ ዜጎችን በልዩ ዘዴ አስገድለውና ገድለው አሁን ደግሞ የቀሩዋቸውን ጥቂት ቅን አሳቢ ዜጎች ለማሰርና ደብዛ ለማጥፋት እየተጉ ነው፡፡ ስለዚህ ዘረኞችን ተክቶ የመጣ የዘረኛ ቡድን የሚያመጣው ውድመት እንጂ ደህና ነገር ባለመኖሩ አንዳችም ለውጥ የለም፡፡ ለውጥ እንዲህ የሚቀለድበት አይደለም፡፡ ለውጥ ቢኖር ኖሮ ስደትና የግፍ ተግባራት በቀነሱ ወይ በጠፉ ነበር፡፡ ለውጥ ቢኖር ኖሮ ርሀብና እርዛት፣ ድንቁርናና ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በተወገዱ ነበር፡፡

ለውጥ አለ እንጂ፡፡ አለሳልሶ ወደ ሥልጣን የወጣው ጠ/ሚኒስትር ወደለየለት አምባገነንነተ እየተቀየረ ነው፡፡ አለው እንለው የነበረውን ዕውቀትና የንግግር ችሎታ ወደጎን በመተው ወደ ብልጠትና የራስን ፍላጎት ለማሳካት በኃይልና በዛቻ ወደመምራት እየተሸጋገረ ነው፡፡ ነገሩ የየጁ ደብተራ ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ ምክንያትና ተጠየቃዊ አካሄድ ሲከዳ ወደጉልበት መዞር የነበረና ያለም ነው፡፡ ሴትዮዋ ልጇ “እማየ ጣቴን አሳከከኝ” ብትላት “እኔም በአንድ ቀን አልተቆመጥኩም” አለቻት ይባላል፡፡ እነመንግሥቱ ኃ/ማርያምም፣ እነቦካሣም፣ እነኢዲያሚንም፣ እነጋዳፊም፣ እነሂትለርም፣ እነሙሶሊኒም፣ እነቢስማርክም፣ እነዚያድባሬም፣ እነካሙዙ ባንዳም፣ እነስታሊንም፣ እነፒኖሼም፣ እነኪም ኢል ሱንግም፣…. በአንድ አዳር አምባገነን አልሆኑም፡፡ አምባገነንነት ቀስ እያለ የሚከሰት የአእምሮ ቁምጥና ውጤት ነው፤ መድኃኒት የሌለው ክፉ የአእምሮ ስንኩልነት ነው፡፡ አቢቹም አፋጠነው እንጂ ወደነዚህ “ሰዎች” ጎራ እንደሚቀላቀል ግልጽ ነበር - መነሻው ትክክል ያልሆነ መገስገሻውና መድረሻውም ትክክል አይሆንም - በወንጀል የተገነባ ስብዕና፣ በተንኮል የተዋቀረ ቁመና በምክንያታዊነት ጥምቀት ስለማያምን ምክንያታዊነትን አምርሮ ይጠላል፤ ምክንያታውያንንም ስለማይወድ አያስቀርባቸውም ብቻ ሣይሆን እየተከታተለ ያጠፋቸዋል፡፡ እየሆነ ያለው ይሄው ነው፡፡

አታሞ በሰው እጅ ታምራለች፡፡ ሲይዟት ግን ታደናግራለች፡፡የሥልጣን ብቸኛ ምንጭ ሕዝብ እስካልሆነ ድረስ፣ በጅዶና በጠረባ በአቋራጭ የሚገኝ ሥልጣን ምን ጊዜም ወደ አምባገነንነት መውሰዱ አይቀርም - አለዚያ አይጸናማ፡፡ ሥልጣን ያሳሳል፤ ወንበር ያጓጓል፡፡ ተማርክ አልተማርክ ዋጋ የለውም፡፡ ዋናው በወደድከው መቁረብህ ነው፡፡ ሥልጣን ከወደደክ ሀገርና ሕዝብ ገደል ቢገቡ ደንታህ አይደለም፡፡ የቀን ቅዠትህና የሌት ቅብዥርህ ሁሉ የሚያቀጣጨው ሥልጣንህን ባለማስነጠቁ ላይ እንጂ ሌላው ሁሉ

ትርፍ ነው፡፡ ስለዚህ በከንቱዎቹ አንፍረድባቸው፡፡ አንዴ አለመለከፍ ነው እንጂ በሥልጣን ሱስ ያበደና የሰከረ ሰው እንኳንስ የምርጫና የሚኒስትሮች መተዳደሪያ ደምቦችን፣ የሀገር የኀልውና አውታሮችን በደቂቃዎች ውስጥ እስከማፈራረስ ሊደርስ ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ ሥልጣን ደግሞ በባሕርይው የተረገመ ነው፡፡ ያንቀዠቅዣል፤ ኅሊናን ያሳውራል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭብጨባ በተለይ በተለዩ ሁኔታ ያሳብዳል፤ ነፈዝ ያደርጋል፡፡ እላይ ስትወጣ ሀብት ንብረቱና ገንዘቡ ብቻ ሣይሆን ዜጎችንም አንተ ራስህ የፈጠርካቸው ሊመስልህ ይችላል፡፡ ስለሆነም ሥልጣኑንም ሆነ ሁሉንም የሀገር ንብረት እናትህ ከጉሊት ገዝታ እንዳመጣችልህ የድንች ጥብስ ለወደድከው ታድለዋህ፤ ለጠላኸው ትነሳዋለህ፡፡ ሁሉም ያንተ ነው፤ ሁሉም ላንተ ያሸረግድልሃል፡፡ ያኔ አንተም ይሞቅሃል፡፡ ራቁትህን ብትሄድ ሁሉም ራቁቱን ይሄድልሃል - ለክብርህ፡፡ ሳያስነጥስህ መሀረቡን የሚዘረጋልህ ብዙ ነው፡፡ኧረ ሚስቱንም የሚጋብዝህና እንድትሾመው ደጅ የሚጠናህም አታጣም፡፡ እኛ እኮ መልካችን እንደነብር ዥንጉርጉር ነው፡፡ ስትወድቅ ግን አንተን አያድርግ፡፡ ያሸቃበጠልህ ሁሉ ቀድሞ ያዋርድሃል፡፡ ጅሎቹ ባለሥልጣናት ያልተረዱት ይህንን መሠረታዊ ሃቅ ነው፡፡

አፄው ግማሽ አምላክ እስከመሆን ደረሱና ተመለኩ፡፡ መንጌ ያቺ ልቡ አበጠችና እንደእፉኝት ተነፋፋ፡፡ መለስ አብጦ አብጦ ንግግሩን ሳይቀር መቆጣጠር አቃተው፤ በዚያም ምክንያት ተቃዋሚዎቹን በሊማሊሞ ሲጠብቅ ሰማያዊ መብረቅ ቀንጥሶ ጣለው፡፡ ዋናው የሁሉም ሁሉም መጨረሻቸው አንድ ሆነ - ውርደት፡፡ ይቺ አቢቹም ከአሁኑ የምትሠራውን አጥታለች፡፡ ኢትዮጵያን በኦሮሞ እየወረረች "በኔ የሥልጣን ዘመን ኦሮሞ የተለዩ ጥቅም አግኝቶ ከሆነ በ24 ሰዓት ሥልጣኔን እለቃለሁ" ስትልም በሣቅ ገደለችን-ቀላል አሾፈች እንዴ!- (አንድ ያስገረመኝን ነገር ልተንፍስ፡- ትናንት አንድ የ8ኛ ክፍል መልቀቂያ የምሥክር ወረቀት አየሁ፤ ሁለት ኃላፊዎች የፈረሙበት ነው፡፡ ሁለቱም ኦሮሞዎች ናቸው፡፡ አጋጣሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ሆን ተብሎ ሁሉንም የኃላፊነት ቦታ ልክ እንደወያኔው ዘመን ሁሉ በተረኛ ዘውግ የመሙላትና ተረኛ ዘውግን የመጥቀም ሌሎችን ደግሞ የማንጓለልና የመግፋት ግልጽ ዘመቻ ነው)፡፡ አቢቹ የጫጫና የደብረ ብርሃን አካባቢ አማራን ትታ "ከሱልልታና ከሰንዳፋ ኦሮሞዎች ጦር ሰብቀው በፈረስ እየተመሙ… እንዴት አድርጌ መፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎቹን ልሰር..?" ብላም አስቃናለች - (መቼ ሰሙና፣ ማን ነገራቸውና)፤ በፊትም ኢንጂነር ስመኘው ራሱን አጠፋ ብላ አስቃናለች፤ በቀደምለትም የምትሠራውን ከሠራች በኋላ በሁሉን ዐወቅ የአተራረክ ሥልቷ ደራሴ-ተውኔት ወተዋናይ አቢይ የባሕር ዳሩን ጭፍጨፋ "የአማራ ክልል መንግሥት ላይ መፈንቅለ መንግሥት ተሞክሮ ከሸፈ" በማለት በአግራሞታዊ ሣቅ ፈጀችን፤ ምን አለፋችሁ ሥራዋ ሁሉ ሁላችንን ማሣቅና ጥቂቶቻችንን ማሳቀቅ ብቻ ሆኖ አረፈው - ምን ይሉኝንም እንክት አድርጋ በልታዋለች - አለመታደል ነው! (አቢይ ግን ከቤተ መንግሥት ይልቅ ለብሔራዊ ትያትር ይቀርባል፤ ደምበኛ ቲያትረኛ አይደል እንዴ! ደሞም ከአሁኑ ትዕቢቷ ("መፈንቅለ መንግሥቱ" ግን ከመጀመሩ መክሸፉ፣ ከመክሸፉም አዲስ አበባ ላይ ለሚገኙ ሁሉን ዐወቅ ሰዎች መፈንቅለ መንግሥት መሆኑና አለመሳካቱ በቅጽበት መታወቁ እናንተዬ! ሕዝብን መናቅ እንዲህ እስከጥግ ነው! ሥልጣን እንዲህ ያባልጋል፤ ያነውራልም፤ ይሉኝታና ሀፍረትንም ከሰውነት አውጥቶ ባዶ ቀፎ ያደርጋል፡፡) ይህን መሰሉ የአቢቹ የሀሰት ክምር አንድም ከትዕቢትና ከትምክህት የሚመነጭ ነው፤ አንድም ዜጎችን በአላዋቂነት ከመፈረጅ የሚበቅል ገለባነት ነው፤ አንድም ራስን ካለማወቅና ለራስ የተለዩ ቦታ ከመስጠት ታላቅ ድንቁርና የሚፈልቅ ነው፤ አንድም ሀሰትን እንደባሕርይ ልብስ ከመውሰድ የሚመጣ ነው - መለስን "pathological liar ነበር" እንደምንለው ፡፡ እውነቱን እኮ ራሱ አቢይም ያውቀዋል፡፡ አይደለም የአሁኑን እውነት ቀጥሎ የሚመጣውን እውነት ሳይቀር ውስጠ ውሳጤው ያውቀዋል - (his subconscious, I mean)፡፡ ሥልጣን እንዲህ ነው፡፡ ድብን አድርጎ ያሳውራል፡፡ እላይ ያለው እንዲህ እንደጣቃ የሚተረተር ከሆነ ከርሱ ቀጥሎ ያሉትማ እንዴት ይሆኑ? አዎ፣ ቤት ጣራው ካፈሰሰ ማገሩና ወጋግራውም መፍረክረኩ አይቀርም፡፡ ወዮልን!

የማያድግ ልጅ ካካው ብዙ ነው፡፡ ሌላም ልጨምርልህ፡፡ የማያድግ ልጅ በአባቱ ብልት ይጫወታል፡፡ ልሰልስልህ ከፈለግህ፡፡ "አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የባሏን መጽሐፍ አጠበች"፡፡ ይህ ሁሉ ምሣሌያዊ አባባል በአንድ ወይ በሌላ መልክ ለአቢቹ ይገጥማል፡፡ ጥሩ ነው፡፡ አቢይ ብዙ ጊዜ ያለው አይመስለኝም፤ ነገረ ሥራውም ይህን ከመረዳት የመነጨ ይመስላል፡፡ ጥድፊያ ያበዛል፡፡ አንዳንዴ እንዳባባ ታምራትም መሆን ይቃጣዋል - በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ የመከሰት ዓይነት ተዓምራዊ ድርጊቶች ያስደስቱታል- በዚያውም ተከታዮችን ማስደመምና ማስጨበጨብ፡፡ ለነገሩ ይፍጠን፡፡ ፍጠን በሉት፡፡ የሚጠቅመውን በቶሎ ይጥቀም፡፡ የሚያስወግደውንም በቶሎ ያስወግድ፡፡ ‹ባለቀ ጊዜ አትዘናጋ› በሉት፡፡ የሁሉንም ሂሣብ ግን በቅርብ ያወራርዳል፡፡ ወያኔም ....

ስለወያኔማ ይህችን ብዬ ልሰናበት እንጂ፡፡ በአንድ ተራራ ላይ ከሚኖሩ ቤቶች በአንደኛው እሳት ይነሳል፡፡ ጎረቤቶች እሳቱን ለማጥፋት በአፈርም፣ በቅጠልም፣ በውኃም … ባላቸው ነገር ሁሉ መረባረብ ይዘዋል፡፡ ከተራራው ግርጌ አንድ ኩሬ አለ፡፡ በዚያ ኩሬ ከሚኖሩ ዕንቁራሪቶች መካከል አንዷ ቀበጥ ዕንቁራሪት እሳት የሚያጠፉትን ሰዎች ሽቅብ እየተመለከተች በማፌዝ መልክ ታሽካካ ይዛለች፡፡ አንዷ አሮጊት ዕንቁራሪት ግን "ምን ሆነሻል አንች ልጅ? ዝም አትይም? ግፍ አታኑሪ"ብላ ትገስጻታለች፡፡ ልጂት ግን "እንዴ እኔ ውኃ ውስጥ እያለሁ ምን እሆናለሁ?" በማለት በተቸገሩት ሰዎች እያላገጠችባቸው ማንቋረሯን ትቀጥላለች፡፡ መንደርተኞቹ በአካባቢያቸው የሚገኘን ነገር ሁሉ ጨርሰው በባልዲ ውኃ ለመጨለፍ ወደዚያ ኩሬ ወረዱ፡፡ ሌሎቹ ወደኩሬው ውስጠኛ ክፍል ወርደው በመሸጎጥ ራሳቸውን ከአደጋ ለማውጣት ሲሞክሩ ያቺ ለፍላፊ ግን በመጀመሪያው ባልዲ ተጠልፋ የእሳት ማጥፊያ ሆነች፡፡ አያድርስ ነው፡፡ ኦህዴድ/ኦነግ አማራን ለመጨረስ ያብቃቸው እንጂ እርሱን ከጨረሱ በኋላ የጎሣ ፖለቲካቸውን

ጦር ዒላማ ወዴት እንደሚያዞሩት ለማወቅ በግድ አሮጊት ዕንቁራሪት መሆንን አይጠይቅም፡፡ ከሁለት ጠላቶች ጋር መፋለም አዋጭ ባለመሆኑ እንጂ ትግሬ ከአማራ ያነሰ ጠላት መሆኑን ከመረዳት አይደለም የኦነግ ሕወሓትን “መታገስ”፡፡

በኢትዮጵያ የሚገርም ሞኘነት እየተስተዋለ ነው፡፡ ሁሉም ቢስማማና ቢተባበር በግሩም ሁኔታ ደልቶት መኖር እየቻለ እንደ እናት ገዳይ እየተያዩ አንዱ ከአንዱ በየተራና በሤራ ፖለቲካ መናቆር የሚያስደንቅ ድንቁርና ነው፡፡ ለነሱ ይሄኔ ዘመናዊነትና ብልኅነት ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ግን ጭልጥ ያለ ገልቱነት ነው፡፡ ዛሬ ቦምብ የምታጠምድለት ወገን ነገ ላንተ ወርቅ አንጥፎና የዘምባባ ዝንጣፊ ይዞ አይጠብቅህም፡፡ የሚያዋጣው በንጹሕ ልብ ቅራኔን አስወግዶ ተከባብሮና ተስማምቶ መኖር ነው፡፡ ይህን የምለው ለቅን አሳቢዎች እንጂ ለአጋንንቱ አይደለም፡፡ ምክንያቱም መጥፎ ልማድ ካላስቀበረ አይለቅምና ሕወሓትንና ኦህዴድን ለመምከር መቃጣት ድንጋይ ላይ ውኃ እንደማፍሰስ ነው፡፡ ተልእኳቸው ልዩ ስለሆነ ሆዳቸው ተገልብጦ ካልተሰፋና በቂም በቀልና ጥላቻ የደነደነው ልባቸው በፍቅር ሞረድ ለስልሶ ካልተስተካከለ  በስተቀር ደግ የማሰብ ፍላጎታቸው ዜሮ ነው፡፡